# የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ

የዚህ ጽሑፍ አላማ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሰሊጥ ምርትና ግብይት መረብ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ግምት ውስጥ በማስገባት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በተመለከተ ለባለድርሻና አጋር አካላት አጫጭር ወቅታዊ መረጃዎችን ማድረስ ነው።

## የግብርና ሜካናይዜሽን የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ስርጭትን ለመቀነስ አስተዋፅኦ ያደርጋል

የኮሮና ወረርሽኝ በመከሰቱ ምክንያት የቀን ሰራተኞች እንቅስቃሴ የተገደበ እንዲሆን አድርጓል። በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ሰሊጥ አምራች አካባቢዎች በሰራተኛ እጥረት ምክንያት የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ መቸገራቸዉ እየታየ ነዉ። ሰሊጥን ለማምረት ለአንድ ሄክታር እስከ 70 የቀን ሰራተኛ ጉልበት ያስፈልጋል። ይህ ቁጥር በሰሜን ምዕራብ አትዮጵያ በየአመቱ በሰሊጥ ከሚሸፈነው የመሬት መጠን (500,000 ሄክታር) አንጻር እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የቀን ሰራተኛ እንደሚያስፈልግ ያሳየናል።፡ በዚህ ወቅት የሚጠበቀውን ያክል የቀን ሰራተኛ ማሰማራት ደግሞ ወረርሽኙን እንዲስፋፋ በር ሊከፍት ይችላል። ወትሮም ችግር የነበረው እና ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘ ሊቀንስ የሚችለውን የሰራተኞች አቅርቦት ችግርን ለመቀነስ፣ የምርት ወጪን የተሻለ ውጤታማ ለማድረግ እና የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ሜካናይዜሽን መጠቀም ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

የግብርና ሜካናይዜሽን ሲባል ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ ምርት መሰብሰብ እና የድህረ ምርት ተግባራትን ያጠቃልላል። እንደሚታወቀዉ ለዚህ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተሞክረዉ መለየታቸዉ እና በተወሰኑ አምራች ባለሃብቶች፤ የአርሶ አደር አገልግሎት ሰጪ ማዕከላት እና አስመጪዎች መኖራቸዉ ይታወቃል። እነዚህን መሳርያዎች አርሶአደሮች በተለይ በዚህ በኮሮና ወረርሽኝ ወቅት በስፋት እንዲጠቀሙባቸዉ ለማድረግ በትግራይ ክልል የሰሊጥ አብቃይ አካባቢዎች ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

በትግራይ ክልል የሰሊጥ አምራች አካባቢዎች የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሜካናይዜሽን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል ማማየ ግሩፕ የእርሻ መሳሪያዎች አስመጭ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ በያዝነዉ የምርት ዘመን እስከ 1,200 ሄክታር መሬት ከባለሃብቶች ጋር በኮንትራት ስምምነት በማድረግ የማሳ ማፅዳትና የእርሻ ሥራ በሜካናይዜሽን እያከናወነ



ይገኛል። በተጨማሪም ሂዎት እርሻ ሜካናይዜሽን የግል ኩባንያ ከባለሃብቶች እና አነስተኛ ይዞታ ካላቸው አርሶአደሮች ጋር ለመስራት በዝግጅት ላይ ይገኛል። በተመሳሳይም ደስታ በርሄ የገበሬዎች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ለአነስተኛ አርሶአደሮች የሜካናይዜሽን ስራ ለመስራት ከግብርና ባለሞያዎች ጋር በመተባበር የአርሶአደሮች መረጣ እያከናወነ ይገኛል። ከነዚህ በተጨማሪም የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት፤ ባለሃብቶች እና ሁመራ ግብርና ምርምር ማዕከል ውስንነት ቢኖረዉም የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ እና አገልግሎት ሰጪዎች ናቸዉ።

እነዚህ አካላት ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረጉ ቢሆንም እንደ መኮትኮቻና ማጨጃን የመሳሰሉ ማሽነሪዎች አለመኖርና የፋይናንስ እጥረት አገልግሎታቸውን በተፈለገው መጠንና ጥራት እንዳያካሂዱ እንቅፋት እየሆኑባቸው ይገኛል። እነዚህ መሳርያዎች በጎረቤት ሃገር ሱዳን እንደሚገኙና በያዝነዉ የምርት ዘመንም እነዚህ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ባለሃብት አርሶአደሮች ልዩ የፋይናንስ ድጋፍ ተደርጎላቸዉ በተለይ መኮትኮቻ እና የሰሊጥ ማጨጃ ማሽኖች ቢያስገቡ የቀን ሰራተኛ ቁጥር በመቀነስ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት እየተደረገ ላለው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። በዚህም ሀገራችን ከሰሊጥ የምታገኘው ምርት እና የውጭ ምንዛሬ እንዳይቀንስ ማድረግ ይቻላል።

## ከኮኖና ቫይረስ ወረርሽኝ እራስዎን ይከላከሉ!




እጅዎን በንጽህ ውሃና በሳሙና ይታጠቡ ወይም አልኮል ባለው የጀርም ማጽጃ ያጽዱ



እጅዎን ሳይታጠቡ አፍዎን፣ አፋንጫዎንና አይንዎን አይንኩ



በእጅ መጨባበጥን ያቁሙ




ከሰዎች ጋር የሚኖርዎትን አካላዊ ርቀት ይጠብቁ

ከነዚህ በተጨማሪም መንግስትና የጤና ባለሙዎች የሚሰጧቸውን ሌሎች መመሪያዎች ይከተሉ!

## የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በአገልግሎት እና በግብርና ዘርፍ ላይ የሚኖረዉ ተጽዕኖ

የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ ተጽዕኖ ዘርፈ-ብዙ እና ሁሉንም የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች የሚገድብና ከፍተኛ ኪሳራ እያመጣ የሚገኝ ችግር ነዉ። ለምሳሌ የሀገራት የንግድ ግንኙነት መወሰን፣ ምግብ ነክ የሆኑና ያልሆኑ ምርቶች፤ መድሃኒቶች እንዲሁም እጅግ አስፈላጊ ጥሬ ዕቃወች እና መሰል አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማስመጣትና መላክ የተገደበ ሁኗል:: እነዚህ ሁኔታዎች በተለይም ኑሮአቸዉ ከእጅ ወደ አፍ የሆኑ ዝቅተኛ የህብረተሰብ ክፍሎች ይበልጥ ተጎጅ እንዲሆኑ ያደርጋሉ:: ጥናቶች እንደሚያሳዩት በዚህ ወቅት በዓለም ዙሪያ ከ95 ሚሊዮን ሠራተኞች በላይ ሥራ አጥ ሆነዋል። ይህን ችግር ለመቅረፍ እና ነገሮችን ወደ ነበሩበት ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል። በዚህ ከባድ ችግር ውስጥ ያልታዩ መልካም እድሎችን በመፈለግና በመጠቀም፤ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መሻሻል በሚያመጡ ስራዎች ዙሪያ በመረባረብ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማድረግ የሁሉም ዜጋ ሀላፊነት ነው።

ምንም እንኳ የሃገራችን የግብርና ዘርፍ አሁንም ድረስ ኋላቀር እና ያልዘመነ መሆኑ የራሱ የሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ቢኖረዉም ወረርሽኙ ሙሉ በሙሉ ስራ እንድናቆም አለማስገደዱን እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ጠንክረን ልንሰራና ምርታማነትን ልናሳድግ ይገባል። የግብርናው ዘርፍ ከሚፈጥረዉ ሰፊ የስራ እድል እና ለኢኮኖሚያችን ከሚየደርገው አስተዋጽኦ አኳያ ትልቅ ትኩረት የሚያሻ ጉዳይ ነዉ። ግብርና የሚመለከተዉ ሁሉንም የሃገሪቱን ህዝብ ነዉ። "ሁሉም ሰዉ ምግብ ያስፈልገዋል! ይህ ማለት ሁሉም ሰዉ ያገባዋል ማለት ነዉ"። በዚህ ዘርፍ ተዋናዩ ብዙ ነው። የግብርና ባለሙያዉ፣ ተመራማሪዉ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማራው፣ አስተዳደር ሰራተኛዉ፣ የሚዲያ ባለሙያዉ የጤና ባለሙያዉ ወ.ዘ.ተ ሁሉም የራሱ የሆነውን ሚና በብቃት በመጫዎት ለሃገር እና ለህዝብ አስተዋጽኦ ለማበርከት መትጋት የሚጠበቅበት ወቅት ነው።

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል በሰሊጥ እሴት ሰንሰለት ዉስጥ ከፍተኛ ድርሻ አና አስተዎጽኦ ያላቸዉ የቀን ሰራተኞች በሙሉም ይሁን በከፊል በታወጀው የእንቅስቃሴ ገደብ እንዲሁም ራሳቸው በቫይረሱ ላለመጠቃት ካላቸው ስጋት ወደስራ ላይሰማሩ ይችላሉ። ከዚህ አንጻር ሰራተኞቹም ሆኑ ሰሊጥ አብቃይ አርሶአደሩ የችግሩ እኩል ገፈት ቀማሽ ይሆናሉ። ይህ ሁኔታ ሥራ አጥነትን ከማስፋፋቱም ባሻገር ምርታማነትን በመቀነስ የምግብ እጥረት እንዲኖር ያደርጋል። ቀስበቀስም ችግሩ የሁሉንም ቤት ያንኳኳል። እነዚህን ተያያዥ ችግሮች ለመቅረፍ ከወዲሁ በንቃት በማሰብና በትብብር መስራት የየድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

### አጋጣሚወችን እንጠቀምባቸዉ

- በዚህ ወቅት ከወረርሽኙ ጋር ተያይዞ የሰራተኛ እንቅስቃሴ መገደቡ የቤተሰብን ጉልበት በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን በነበረዉ መልኩ ለማስቀጠል እና ከብክነት ለማዳን በሃላፊነት የግብርና ስራ ላይ ርብርብ ማደረግ
- በወረርሽኙ ምክንያት ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸው ቤት የሚዉሉ ተማሪዎች ያላቸዉን ትርፍ ጊዜ ግብርና ስራ ላይ ማዋል ይችላሉ።
- እንዲሁም ሴት ተማሪዎች እና ዕድሜያቸዉ ስራ ለማገዝ የሚፈቅድ ህጻናት በጓሮ አትክልት እና ፍራፍሬ ልማት ላይ በመሰማራት ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ። ለዚህም ጥሩዉ አጋጣሚ በቂ የመንከባከቢያ ጊዜ መኖሩ እና በመጭዉ የክረምት ወቅት የዉኃ እጥረት ባለመኖሩ እንደ መልካም አጋጣሚ መጠቀም ያስፈልጋል።
- እንደ ወንፈል እና ደቦ የመሳሰሉ ማህበራዊ የትብብር ስራ ባህሎችን በመጠቀም አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ እየተከተሉ በመተጋገዝ የቀን ሰራተኛ አቅርቦት ችግርን መቀነስ ያስፈልጋል::
- በርካታ ቁጥር ያላቸው በከተማ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በትርፍ ጊዜያቸው አቅሙ እና ሁኔታው በሚፈቅድላቸዉ መጠን በጓሮ አትክልት ልማት ስራ ላይ በትንሽ መጠን ቢሰማሩ በብዙ መልኩ ተጠቃሚ ይሆናሉ::

## ለአኩሪ አተር ምርጥ ዘር ፈላጊዎች

በአማራ ክልል የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ወይም የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ምስረታ ጋር በተያያዘ የአኩሪ አተር ምርት በከፍተኛ መጠን እንደሚፈለግ እየተገጸ ነው።ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት የጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል ለመጭው የምርት ዘመን የሚሆን ጥራት ያለው የአኩሪ አተር ምርጥ ዝርያ (በሄክታር ከ20-24 ኩንታል መስጠት የሚችል) ከ140 ኩንታል በላይ ስለአዘጋጀ ዘር አምራቾች፣ አርሶአደሮች፣ ባለ ሃብቶች፣ የግል ድርጅቶች እና ለሌሎች አካላትም በማዕከሉ ግቢ በግኝ ያቀረበ መሆኑን ይገልጻል።





## በድርብርብ (ቆጥ) የጓሮ አትክልት ልማት



የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን (ኮቪድ-19) ለመከላከል እንደ አንድ የመፍትሔ እርምጃ እየተወሰደ ያለው የሰዎችን እንቅስቃሴ መግታት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በጣም ለአስፈላጊ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ሰዎች ከቤታቸው እንዳይወጡ ይመከራል፡፡ በዚህም ምክንያት በበርካታ ሀገራት ሰዎች ብዙ ጊዜያቸውን ቤት ውስጥ በመቀመጥ እያሳለፉ ይገኛሉ:: ይህ ጉዳይ በእኛም ሃገር በከፊልም ቢሆን እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ሰዎች ጊዜያቸውን በቤታቸው ሲያሳልፉ እራሳቸውን ከወረርሽኙ ከመጠበቅ ባሻገር በተለይ በመኖሪያ ቤታቸው ዙሪያ ቦታ ያላቸው አትክልት በማልማት ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው ንጹህ የሆነ ምግብ መመገብ ይችላሉ፡፡

የጎንደር ግብርና ምርምር ማዕከል በጓሮ የሚገኝ ትንሽ ቦታን በመጠቀም እንዴት አትክልት ማምረት እንደሚቻል ለማሳየት በማዕከሉ ግቢ የድርብርብ(ቆጥ) ግብርና አሰራርን እየተገበረ ይገኛል፡፡ ይህ በፎቶግራፉ የምትመለከቱት ሥራ አገልግሎት የሰጡ የፕላስቲክ ጠርሙሶችን፣ የቀለም ቆርቆሮዎችን፣ የማዳበሪያና የሲሚንቶ ከረጢቶችን በመጠቀም እንዲሁም በእንጨትና በጣውላ ርብራብ በመስራት አትክልቶችን እንዴት በቀላሉ ማምረት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው፡፡

የጎንደር ግብርና ምርምር ዳይሬክተር አቶ አስፋው አዛናው እና በማዕከሉ የአፈርና ውሃ ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ባዬ አያሌው እንደገለጹት ይህ የሙከራ ስራ በዚህ ወቅት ሰዎች ቤታቸው ሆነው አትክልቶችን በዚህ አይነት ዘዴ በማልማትና በመንከባከብ ጊዜያቸውን እንዲያሳልፉ፤ ከንክኪ እና ኬሚካል ነፃ የሆነ አትክልት መመገብ እንዲችሉ ከማስቻሉም በላይ የከተማ ግብርና ቴክኖሎጅ ለማስተዋወቅ ይረዳል ብለዋል፡፡ በቀጣይ ዓመትም ከግብርና መምሪያ ጋር በመተባበር የድርብርብ (ቆጥ) ግብርና አሠራርን በጎንደር ከተማ ለማስፋት ዕቅድ መያዙንም ተናግረዋል፡፡ ይህ ስራ በከተማ ለሚኖሩ በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## በአማራ ክልል የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች በቅርቡ ሥራ ይጀምራሉ

በኢትዮጵያ ከተቋቋሙ በርካታ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ዉስጥ የቡሬ ኢንዱስትሪያል ፓርክ አንዱ ነው፡፡ ይህ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለአገሪቱና ለክልሉ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚያስገኝ ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ የግብርናውን እሴት ሰንሰለት በእጅጉ ሊያሻሽሉ የሚችሉና አገሪቱ በጥሬዉ ወደ ዉጭ የምትልከዉን ምርት በመቀየር ለኤክስፖርትና ለሀገር ዉስጥ ፍጆታ ሊዉሉ የሚችሉ ምርቶችን የሚያመርቱ ወሳኝ ኢንዱስትሪዎችን የያዘ ነዉ፡፡ ከእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ሪች ላንድና ፊቢላ የተባሉ በኢትዩጵያዊያን ባለቤትነት የተቋቋሙ በዋናነት የአኩሪ አተርና ሰሊጥን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ሲሆን፤ የአርሶ አደሩን የገበያ ችግር በመቅረፍና ለምርቱ የተሻለ ዋጋ በመስጠት፤ እንዲሁም አርሶ አደሩ የገበያ እጦት ችግር ይገጥመኛል ብሎ ሳያስብ በምርቱ ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሰራ በማድረግ የሚኖራቸዉ ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

እነዚህ ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን የጥሬ ዕቃ ያለምንም ውጣውረድ እንዲያገኙና ከአርሶ አደሩ ጋር የግብይት ትስስር እንዲፈጥሩ ማድረግ በዘርፉ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላትና የመንግስት ተቋማት የሚጠበቅ ተግባር ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በቅርቡ ወደ ስራ እንደሚገባ የሚጠበቀዉ ሪችላንድ ካምፓኒ ለግብዓት የሚጠቀምበትን አኩሪ አተር ከአድማስ ዩኒዬን ጋር በገበያ ትስስር ለማግኘት ያደረገው ጥረት በተለያዩ የቢሮክራሲና የአሰራር ችግሮች ምክንያት ብዙም ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ አሁን ባለው አሰራር ዩኒዮኖቹ የሚፈቀድላቸው በኢትዩጵያ ምርት ገበያ ድርጅት መሸጥ ወይም ወደውጭ መላክ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በዘርፉ ውስጥ ተዋናይና አጋዥ ለሆኑ አካላት መፍታት ያለባቸዉ ችግር እንዳለ አመላካች ነዉ፡፡

የሪች ላንድ ካምፓኒ አመታዊ ፍላጎት እስከ1.5 ሚሊዮን ኩንታል ይደርሳል፡፡ ማቀነባበሪያ ፋብሪካው ይህንን ምርት ለማግኘት ይችል ዘንድ የሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ያሉትን የአሰራር ክፍተቶች ገምግመው ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ሌሎች ተመሳሳይ ካምፓኒዎች ያላቸዉ ከፍተኛ የግብዓት ፍላጎት አሁን ባለዉ ሂደት ይፈታል ብሎ መጠበቅ ይከብዳል:: በመሆኑም መንግስት ካምፓኒዎች ከዮኒዬኖችና መሰረታዊ ማህበራት ጋር የግዥ ትስስር የሚተገበሩበትን አማራጭ መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ማድረግ ማህበራቱ ከአቀናባሪ ፋብሪካዎች ለግብዓትና ለግብይት የሚሆናቸውን የቅድሚያ ፋይናንስ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡ አባል አርሶአደሮች በግብይት ወቅት ከማህበሮቻቸው የተሻለ ዋጋ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፤ በዓመቱ መጨረሻም ከማህበሮቻቸዉ የግብይት እንቅስቃሴ የትርፍ ክፍፍል ተጋሪ ይሆናሉ፤ በአጠቃላይ የግብይት ትስስሩ ከማህበራት ጋር ሲሆን የአርሶአደሩን ምርትና ምርታማነት ብሎም ገቢ እንዲጨምር አስተዋጾኦ ያደርጋል፡፡

በሰሊጥ ምርትና ግብይት የተሰማሩ የገበሬዎች ኀብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖችም ከአባል አርሶአደሮቻቸው የሚሰበስቡትን የአኩሪአተር ምርት ጥራት በመጠበቅና የውሳኔ አሰጣጥና አጠቃላይ የአሰራር ሂደታቸውን የተቀላጠፈ በማድረግ ከአቀናባሪ ፋብሪካዎች ጋር ጥሩ የሆነ የንግድ ትስስር ለመፍጠር ጠንክረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

BENEFIT
Bilateral Ethiopian-Netherlands Effort for Food, Income and Trade

SBN